## ሕጉ ምን ይላል ?

በስዊዘርላንድ ግርዛት ህገ ወጥ ተግባር ነው።

ግርዛት የሰውን አካል ለከባድ አደጋ የሚያጋልጥ ድርጊት እንደሆነ ይቆጠራል (122 CP)።
ብሎም የሰውን ጤና በማወክ ህይወትን አደጋ ላይ ሊጥል ይችላል (127 CP)።
ይህን ድርጊት ፈጽሞ የሚገኝ ሰው፥ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት ከስድስት ወር እስከ አስር አመት ሊደርስ በሚችል እስራት ይቀጣል።
ይህ ድርጊት ከስዊዘርላንድ ውጭ የተፈጸመ ቢሆንም እንኳን፤ ልዩ በሆኑ ሁነታዎች የስዊዘርላንድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ተግባራዊ ይሆናል።

አለም አቀፍ ስምምነቶችም ይህን ድርጊት አጥብቀው ይቃወማሉ።

እንዲሁም በአንዳንድ አግሮች መግረዝ በህግ የተከለከለ ነው።

## ምንስ ይደረግ ?

> በቤተሰብዎ መካከል ስለ ግርዛት ሲወራ ሰምተው ያውቃሉ ?

> ወደ ተወለዱበት ወይም ቤተሰብዎ ወደ መጡበት አገር ለመሄድ ይፈራሉ ?

> ጓደኛዎ ግርዛትን አስመክቶ ጭንቀቷን አካፍላዎት ይሆን ?

> የጤና ጥበቃ ሰራተኛ ወይም አስተማሪ ሆነው በሚያገለግለበት ቦታ ስለግርዛት ተጠይቀው ያውቃሉ ?

ይህ ከሆነ በምንም አይነት ለሚመለከተው ክፍል ከማሳሰብ እንዳይቆጠቡ።

ትርጉም ፤ መሠረት ኃይሌ ቢተው

**Service de planning familial et d’information sexuelle**
**Dienst für Familienplanung und Sexualinformation**
**የቤተሰብ አመራር አገልግሎትና የፍትወተ ስጋ መረጃ**

Rue de la Grand-Fontaine 50
1700 Fribourg
T 026 305 29 55
planningfamilial@fr.ch
www.fr.ch/spfis

**Bureau de l’intégration des migrant-e-s et de la prévention du racisme**
**Fachstelle für die Integration der MigrantInnen und für Rassismusprävention**
**የሰደተኞች ማዋሀጃና የዘረኝነት መከላከያ መስሪያ ቤት**

Grand-Rue 26
1700 Fribourg
T 026 305 14 85
integration@fr.ch
www.fr.ch/integration

ETAT DE FRIBOURG
STAAT FREIBURG

2011 Amharique / Amharisch / ሁለት ሺ. አስራአንድ ዓ/ም



# የሴቶች ግርዛት

## የሴቶች ግርዛት ምንድነው ?

የግርዛት ጠቅላላ ያሰራር ዘዴ የሴቶችን ውጫዊ ብልት በሙሉም ሆነ በከፊል ካለምንም የጤና መታወክ ምክኒያት የሚደረግ መቁረጥ ነው። በሌላ መንገድ ለመግለጽ ከዚህ የተለየ ቃላት መጠቀምም ይቻላል።

## ግርዛት እነማንን ነው የሚመለከተው ?

በማንኛውም የእድሜና የመደብ ክልል የሚገኙ የአፍሪካ፣ የመካከለኛው ምስራቅና የእስያ ተወላጅ የሆኑ ወጣትና ትልልቅ ሴቶችን ይመለከታል።

በአፍሪካ ክፍለ አህጉር ብቻ ከሶስት ሴቶች መካከል አንዷ የግርዛት ሰልባ ነች። ዛሬ በብዛት ተሰደው በተለያዩ የአውሮፓ አገሮች ከሚኖሩት ሴቶች የግርዛቱ ሰለባዎች ናችው ተብሎ ከሚገመተው ወደ 7000 ያህለ የሚኖሩት በስዊዘርላንድ ነው።

## የግርዛት መንሳኤው ምንድነው ?

ግርዛት ቅድመ ሃይማኖታዊ የሆነ፡ ማንኛውም ሃይማኖቶች ከመኖራቸው በፊት ሲተገበር የነበረ የአከባቢ ጥንታዊ ልምድ ነው።

ግርዛት በሃይማኖት ተጽኖ የመጣ ነው ብሎ ማመን በፍጹም ሃሰት ነው። በተቃራኒው የትኛውም ሃይማኖት ግርዛትን አይደግፍም።

የተገረዘች ሴት ወላድነቷን ከፍ ያደርገዋል የሚባለው በእውነት ላይ ያልተመሰረተ ነው። በተቃራኒው ግን ሴትን እንድትመክን ሊያደርግም ይችላል።

የተገረዘች ሴት ለባሏ ታማኝና ንጹህ ትሆናለች የሚባልውም ከእውነት የራቀ ነው።

እንዲሁም ግርዛት የሴቶችንና የወጣት ልጃገረዶችን ጤና በከፍተኛ አደጋ ላይ እንድሚጥል ይታወቃል።

## በግርዛት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ ጉዳቶች ?

ባጭርና በመካከለኛ ጊዜ ውስጥ በግርዛት ምክንያት ከሚድርሱት ጠንቆች መካከል፤

ሃይለኛ የሆነና የማይቋርጥ ህመም መሰማት፤ የደም መፍሰስ፤ የማቃጠል ብሎም የመቁሰል ይገኙበታል።

እንዲሁም የምጥ ስቃይ፤ በግብረ ስጋ ግኑኝነት ወቅት ከባድ ህመም ብሎም ስነ ልቦናዊ ቀውስን ያስከትላል።